ይድረስ ለዶ/ር ወንድሙ መኮነን

ለንደን

"ሳያረጋግጡ ወሬ ሳይገድሉ ጎፈሬ"

ዶ/ር ፡ በሀገር ወዳድነትዎ ጨዋ ሰላምታ አሰጣጠዎ በትሑት አነጋገርዎ በአንዳንድ ሕዝባዊ ትይንት አጋጣሚ በአካል አውቅዎታለሁ፤ ከሰው እንደሰማሁት በለንደን ዉስጥ በአንድ ከፍተኛ ዩኒቨርስቲ ውስጥ በመምሕርነት እንደሚሰሩ ሰምቻለሁ፤ ዶ/ር ተብለው መጠራትን እንደ አርቲፊሻል ስለሚቆጥሩት ብዙም እንደማይደነቁበት እርስዎ አጫውተውኛል በዚህም ምክንያት ወንድማችን በማለት እንደምጠራዎ ያስታውሳሉ፡ ከታናሽ ከታላቁ ጋር ተመሳስሎና ተሳስቆ የመኖር ኢትዮጵያዊ ጨዋነት የተመላዎ መሆኑን በእኔ አቅም ለመለካት ችያለሁ።

ይሁን እንጂ " የለንደን ቅድስት ማርያም አድኑኝ ትላለች" በማለት ለሀገራችን ዜጎች የማሕበራዊና ፖለቲካዊ መረጃዎች በሚገኙባቸው ድህረ ገጾች ጽፈው ለንባብ ኣብቅተዋል፤ እኔም እንደማንኛውም ዜጋ ሁሉ የእነዚህ ድህረ ገጾች ትጉህ ተጠቃሚ በመሆኔ "የለንደንዋ ማርያም አድኑኝ ትላለች" የሚለውን የጩኸት ጥሪ ያተቱትን አነበብኩት ጥሩ የቃላት አገባብና የዐረፍተ ነገር አሰካክ ያለው ቢሆንም በርዕስ አመራረጡ በጠቅላላው የጽሑፍ ይዘት ከእውነት የራቀ ሐሰት በመሆኑ አዝኛለሁ።

መቸም በሰለጠነ ዓለም እየኖሩ ያውም በከፍተኛ ተቅዋም ውስጥ በመምሕርነት እየሠሩ ተሳስተዋል የሚለውን ይቃወማሉ ወይም ጠላት ያደርጋሉ ብየ አልገምትም የሚቃዎሙኝ ከሆነ ተሳስተኻል የሚለውን የሚጠላ ውያኔ ነውና እርስዎም ወያኔ ሁነዋል ማለት ነው።

"ሳያረጋግጡ ወሬ ሳይገድሉ ጎፈሬ" ብሂል፡፡ ሀገራችን ኢትዮጵያ እጅግ በጣም አስደናቂ ውብ ባህሎች ፤ ቅርሶችና የታሪክ መረጃዎች እንዳሏት ሁሉ በቋንቋ ደረጃም ቢሆን በጣም የሚማርኩ የሚአዝናኑና በቀላሉ የሚአስተምሩ የአነጋገር ለዛዎች ፤ቀልዶች፤ሰምና ወርቅ እንዲሁም ሰፊውን በጠባቡ ረጅሙን ባጭሩ የሚገለጽበት የአነጋገርብሂሎች አሉ፤ ከነዚኽም ውስጥ ለዚህ ጽሑፍ ርዕስ እንዲሆነኝ የመረጥኩት በኢትዮጵያውያን አርበኞች የሚነገረውን "ሳያረጋግጡ ወሬ ሳይገድሉ ጎፈሬ" የሚለውን የአነጋገር ብሂል መረጥኩና "የለንደንዋ ማርያም አድኑኝ ትላለች" የሚለውን በስሕተት የተሞላ ትንታኔዎን መጠቆም ግድ ሆኖብኛል።

አለዚያ ውሸት ሲደጋገም እውነት ይመስላል ነውና፤ በቀደሙት አርበኞች አባቶቻችን የአርበኝነት ውሎ ያልተጣራ ወሬ/ መረጃ የሰውን ኃይል ፤ ጊዜን፤ ገንዘብን፤ እውቀትን ከማባከኑም በላይ በሰው ልጅ ላይ ፍርድን ያጓድላል ከዚያም አልፎ የሕይወትና የንብረት መጥፋትን በማስከተል በታሪክ የማይረሳ ቁስል ትቶ ያልፋል።

በተጨማሪም በሀገራችን የአርበኝነት ታሪክ በዘማችነቱ በአርበኝነቱ፤ በተኳሽነቱና ጠላቱን አሳዶ በመማረክ ግዳይ በመጣል በቆራጥነቱ፤ በጀግንነቱ፤ በዱር ገደል መንከራተቱ ያልታወቀና ያልተመሰከረለት፤ እንዲሁ በድፍረት እንደአንበሳ ጸጉሩን አጎፍሮ (አቁሞ) ግንባሩን ሽምጥጦ በባዶው ደጃዝማች በላይ ዘለቀን፣ ራስ አበበ አረጋይንና ራስ አሞራው ውብነህን መስሎና ተመሳስሎ

የሚታየውን **አስመሳይና የማጀት አይጥ** የዕውቀት ምንጭ የሆኑት አባቶቻችን “ሳያረጋግጡ ውሬ ሳይገድሉ ጎፈሬ” በማለት ይቆነጥጡታል።

የዶክተር ማዕረግ የለኝም፤ ሆኖም በቤተክርስቲያናችን መንፈሳዊ አስተዳደር የተሻለ ግንዛቤ ፣ የስራ ልምድ ወይም ከመንፈሳውያን አባቶች ጋር ውየ አድሬአለሁ የሚል እምነት አለኝ፤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ከማፍቅረው እምነቴ ባሻገር ለሀገራችን ኢትዮጵያ በማኅበራዊ ኑሮ የእውቀት፤ የስልጣኔ፣ የአስተዳደርና የመሪነት ምንጭ ሁና ያደረገችው ግዙፍ አስተዋጽኦ በቃላት ተነግሮ የሚአልቅ ካለመሆኑም በላይ፤ በዚህች ቤተክርስቲያን ውስጥ ያለፉት ሊቃውንት የታሪክ አሻራ አሁንም በመንፈሳዊ ትምህርት ያለምንም ድጎማ የደከሙትን ሳስታውስ የሚሰማኝ ሰቆቃ ከፍተኛ ነው። እናቶቻችን ለእነዚህ ሊቃውንት ዋጋ ከፍለውበታል፤ በእንተማርያም ብሎ ሲለምን፤ በእንጨትና በጢስ ካበሰሉት ከልጆቻቸው ጉረሮ አካፍለው በማብላት በማጠጣት ለረጅም ዓመታት በማስተማር ቤተክርስትያናችንን ጠብቀው በማስጠበቅ እዚህ ደረጃ አድርሰዋታል። በጠቅላላው ለዚህች አማናዊት ቤተክርስትያን ያለኝ ፍቅር ከፍተኛ መሆኑን ባጭሩ ልገልጽልዎት እወዳለሁ።

ከዚህ ቀትሎ ብዙ ታሪክ ሳላበዛ “ የለንደንዋ ማርያም አድኑኝ ትላለች” በማለት በጻፉት የታዩትን ስህተቶች ከዚህ እንደሚከተለው እጠቁማለሁ።

__ስህተት አንድ__

“ የለንደንዋ ማርያም አድኑኝ ትላለች” እምነት ያለው ሰው ስለእምነቱና ከእምነቱ ጋር በተያያዘ ጉዳይ በሚናገራቸውና በሚጽፋቸው ነገሮች ሁሉ በእጅጉ መጠንቀቅ አለበት፣ ማገናዘብ፣ ማንበብና መጠየቅም የግድ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንደዚህ ይመክረናል “ አባትህን ጠይቅ ይነግርሃል፣ ሊቃውንትን ጠይቅ ያሳውቁሃል “ ዘዳግ. 32፤ 7. ይህን የመጽሐፍ ቃል በትርጓሜ የተረዱትና የተማሩት አበው “መጠየቅ ያደርጋል ሊቅ” በማለት እረጅሙን ባጭሩ ይገቱታል/ ይገልጹታል አለዚያ በድፍረት፣ በማናለብኝነትና በስማበለው የሚጻፍ ነገር ሁሉ ስቶ ማሳት ይባላል።

እናታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ቅድመ ዓለም በአምላክ ኅሊና ታስባ የነበረች በኋላም እግዚአብሔርን ፈሪ ሰውን አክባሪ በፍቅር ከሚኖሩ ለጸሎት ከሚተጉ ከእናቷ ከሐና ከአባቷ ከኢያቄም በጸሎት (ከእግዚአብሔር ጋር በተደረገ ግንኙነት) በልመና በስእለት የተወለደች ለቤተክርስትያን አስራት የተሰጠች፣ በብስራተ ቅዱስ ገብርኤል በመንፈስቅዱስ ግብር የዓለም መድኃኒት አምላክ ሰው ሰው አምላክ ሆኖ በስጋ የተወለደባት፣ ከመውለዷ በፊት ድንግል ከወለደች በኋላ ድንግል ያማላጅነት ሀብት የተሰጣት ከፈጣሪ በታች ከፍጡራን በላይ የሆነች ወላዲተ አምላክ ናት።

እኛ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስትያን አማኞችና ተከታዮች በአማላጅነቷ እንድናለን ድነንማል።

ታዲያ “የለንደንዋ ማርያም አድኑኝ ትላለች” በማለት የጻፉት መቸ ስትጮኽ ሰሚት? እንዴትስ ሰሚት? ቤተክርስትያን ውስጥ ካየሁዎት ካራት ወር በላይ ሆኖኝአል፤ በሕልም ነው ወይስ በውን? እሷ የእኛን አዳኝነት የምትጠይቅ፣ የሚአስፈልጋት፣ የምትለምን ከሆነ የእኛ በአማላጅነቷ ማመን፣ መታሰቢያዋን ማክበር፣ ሕንጻ በስሟ ማሰራት (መግዛት) ለምን አስፈለገ? በመሆኑም “የለንደንዋ ማርያም አድኑኝ ትላለች” የሚለው ቃል ብቻውን ከአንድ የሃይማኖት ተቆርቋሪ ነኝ ከሚል ሰው የሚወጣ አይደለም፤ ይህ ቃል ብቻውን ራሱ በራሱ “ስቶ ማሳት” ነው። ይህን እንደአርዕስት ተጠቅሞ እነ ሊቀጠበበት አለማየሁን በማይረባ ነገር ልቦናቸውን ከማሻከር ይልቅ መጠየቅ ተገቢ ነው። ባይሆን “ሕንጻ

ቤተክርስቲያኑ አድኑኝ ይላል" ብለው **ድንጋዩን ወክለው ቢጽፉ የተሻለ ነበር።** እሱም ግዑዝ ነው፤ አይናገርም፤ ታዲያ የማንን ጩኸት ነው የሰሙት? መልሱን እኔ እመልሳለሁ።

"አድኑኝ እያሉ የሚጮኹት ቅድስት ማርያም ሳትሆን ጌታቸው በሻህውረድና ሻለቃ ማሞ ናቸው። የለንደንዋ ማርያም ማለት እነሱ ናቸው ብለው ካመኑ መብትዎ ነው። ነገር ግን ሳያረጋግጡ ወሬ ይሆንብዎታል።

## ስህተት ሁለት

በግንቦት 1997 ዓ፡ም የሀገራችን ሕገ መንግስት በሚፈቅደው መሠረት በተለይም የአዲስአበባ ኗሪ ሕዝብ በሙሉ በስልጣን ላይ ያለውን ገዥ መደብ በመቃወም በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ አስደናቂ የሆነ የተቃውሞ ሰላመዊ ሰልፍ በማድረጉ ምክንያት 193 ንጹሐን ዜጎች በግፍ በመገደላቸው፣ የአዲስአበባ ዩኒበርስቲ ተማሪዎች ከተጠጉበት ቤተ ክርስቲያን ተላልፈው ለወያኔ ወታደሮች በመሰጠታቸው የለንደኑ ሕንጻ ቤተክርስቲያን እንዳይገዛ በማገዳቸው ምክንያትና በመሳሰሉት ምክንያቶች ሁሉ የአቡነ ጳውሎስን ስም በጸሎተ ቅዳሴ አንጠራም፤ እሳቸውም እስካሉ ድረስ በምንም ዓይነት የፓትርያርኩን ትእዛዝ አንቀበልም በማለት በቃለ ጉባኤ ይዘው ውሳኔ አሳልፈው የተፈራረሙ ካሕናት በሙሉ መሆናቸው እርግጥ ነው። ነገር ግን በዚህ ውሳኔ ውስጥ የእርስዎም ሆነ የጌታቸውና የሻለቃ ማሞ ስምና ፊርማ የለም፤ ነገር ግን ይህ አቋም በእርስዎና በጓደኞችዎ ብቻ እንደተወሰደ አስመስለው ማራገብና የጀግና ታሪክ መተረክ አግባብ አይደለም። "ሳይገድሉ ጎፈሬ" ማለት ይህ ነው።

## ስህተት ሦስት

ሊቀጠበብት አለማየሁ ደስታ "እኛ የቅዱስ ሲኖዶስ ነን፣ የቤተክሪስቲያን ሀብትና ንብረት የቅዱስ ሲኖዶስ ነው በማለት "የለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን ሀብትና ንብረት በወያኔ ሥር ለሚታዘዘው ቅዱስ ሲኖዶስ ለንደን በሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ አማካኝነት ለያስረክቡ ነው" በማለት ወቅሰዋል። ዘልፈዋል።

ሊ/ጠበብት አለማየሁ ደስታ በቤተክርስትያናችን መንፈሳዊ ትምህርት በሁለንተናዊ መልኩ ብቃት ያላቸው የጉባኤ መመህር ናቸው። በተፈጥሮአቸው ተዕቢትን የሚንቁ ብዙ ከበሬታን የሚጠሉ በዋዛ በፈዛዛ ባለባሌ ቦታዎች የማይገኙ ቁጥብ እውነተኛ የቤተክርስቲያን ልጅ ናቸው።

በለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተክርስትያን ከአሥር ያላነሱ ዲያቆናትን በማስተማር ዛሬ ቤተክርስቲያንን ነቅተውና ተግተው የሚአገለግሉ የእሳቸው ደቀ መዛሙርት ናቸው። ይህም ማለት በስደት ሀገር ትውልድን የማነጽ፤ ሃይማኖትንና ታሪክን የመጠበቅ ተምሮ የማስተማር ኃላፊነታቸውን እየተወጡ የሚገኙ የቤተክርስትያን መንፈሳዊ መምህር እንጂ የፖለቲካ ሰው አይደሉም።

በመሆኑም ጥብቅናቸው ለሃይማኖት መሆኑን ጠንቅቀው ስለሚአውቁ አቋማቸውን በፊርማ ካረጋገጡት መካከል አንዱና ዋነኛው ናቸው። ይህ እየታወቀ "የቤተክርስትያኑን ሀብትና ንብረት ለክርስቶስ ላልሆኑ ሰዎች አሳልፎ ሊሰጥ ነው" በማለት ስም ማጥፋት ስህተት ነው። ሐሰትም ነው። እርግጥ ነው ቤተክርስቲያን ባለው መንግስት ምክንያት ለሁለት መከፈሏ፤ መንግስት ይታሪክና የሀገር ባላደራነትዋን ቀምቶ፤ ተከታዮቿን በጎሳ ለያይቶ ከፍተኛ በደል አድርሶባታል። በዚህም ምክንያት የለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን ካህናትና ምእመናን ከቅዱስ ሲኖዶስ ጋር የማይከሰስና የማይገሰስ የሃይማኖት መንፈሳዊ ግንኙነት እንጂ የአስተዳደር ግንኙነት ተቋርጧል። እስከ አሁን በዚሁ አቋም ጸንታ ትገኛለች።

ይሁን እንጂ ቤተክርስቲያን ወደቀደመ ክብርዋ ተመልሳ በውስጥና በውጭ እንዲሁም "ገለልተኛ" ነኝ ከሚል በታሪክ ታይቶ ከማይታወቅ ክፍፍልና የታሪክ በሽታ ተፈውሳ ወደአንድነትዋ ከተመለሰች በእርግጥ ሊቁ እንደተናገሩት የምናገለግልበት የምንገለገልበት ክህነት፣ የሃይማኖት መመሪያዎችና መንፈሳዊ መዋቅሮች እንዲሁም የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረት በቅዱስ ሲኖዶስ የበላይ መሪነትና ባለቤትነት የሚመራ መሆኑን ልናረጋግጥ እንወዳለን።

የደብሩ አስተዳዳሪ መ/ጽ አባ ግርማ ከበደ በደብሩ ውስጥ ስብከተ ወንጌል እንዲስፋፋ፣ ሕንጻ ቤተክርስትያን እንዲገዛ፣ ነጋ ለኪዳን መሸ ለቁርባን ለቤተክርስትያን መንፈሳዊ አገግሎት የሚተጉ ከመሆኑም በላይ ከላይ የተጠቀሰው አቋም እንዲወሰን በሰብሳቢነት የመሩ፣ ውሳኔው ተግባራዊ እንዲሆን በአስፈጻሚነት የሰሩ፤ አሁንም እያስፈጸሙ የሚገኙ ናቸው እንጂ ከዚህ ውጭ የቤተክርስትያኑን ንብረት አሳልፎ ለመስጠት የተደራደሩበት የሚደራደሩበት ምንም ዓይነት ማስረጃ የለም፤ ፍጹም ሐሰት ነው።

በመሆኑም ዶ/ር ወንድሙ በስማ በለው የጻፉት የጌታቸውንና የሻለቃ ማሞን የአድኑኝ ጩኸት ሰምተው እንጂ ቅድስት ማርያም አድኑኝ አላለችም፤ ልትልም አትችልም። ሐሰት ነው።

<u>ማጠቃለያ</u>

"አድኑኝ " በማለት የሰሙት ጩኸት የቅድስት ማርያም አይደለም እርግጥ ነው እሷ የእኛን አዳኝነት አትፈለግም ነገር ግን የሰሙት የአድኑኝ ጩኸት የጌታቸውና የሻለቃ ማሞ ነው። የምን ጩኸት? ለሚሉኝ ጥያቄ መልስ መስጠት ግድ ነው።

የምን ጩኸት ለሚለው ጥያቄ የሐሰት ጩኸት ስም ለማጥፋት ነው። ለምን ጮኹ ለሚለው ደግሞ ቤተክርስቲያን ኃላፊነቱ በተወሰነ የግል ኩባንያ ካልተመዘገበች፣ በካንፓኒ ሕግ ካልተመራች፣ በዲሬችተሮች ካልተገዛች በእንግሊዝ ሀገር ሕግ አትታወቅም፤ ሀብትና ንብረቷ ቢጠፋ ተጠያቂ የለም፤ ሊአድናትና ሊጠብቃት የሚችል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባንያ ብቻ ስትሆን ነው፤ መንፈስቅዱስ የሚባል የበላይ መሪ አናውቅም፤ የሚል ጩኸት ነው።

ይኸ ጩኸት ደግሞ በካህናቱ በኩል ዶ/ር እንደሰሙት ተሰሚነት አላገኘም፤ የማርያም ጩኸት ሁኖ አልተገኘም፤ ቤተክርስትያን የእንግሊዝ ሀገር ሕግን አክብራ በስደት እንድትኖር ትገደዳለች እንጂ፣ የእርሷን ሕግጋት አፍርሳ፣ መንፈሳዊ ማንነቷን ጥሳና ሃይማኖታዊ ስያሜዋን ለውጣ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባንያ ሆና በዲሬክተሮች የበላይነት እንድትመራ የሚአስገድድ አንድም ነገር የለም። በካምፓኒ ሕግ የበላይነት ካልተገዛችሁ አትኖሩም አላሉም። የነርሱ ካቶሊካዊት ቤተክርስትያንና የአንግሊካን ቤተክርስትያን በካምፓኒ ሳይመዘገቡ እኛ ለምን የግል ኩባንያ ቅኝ ተገዥነት ፍቅረኞች አደረገን?

ይህን ለመመለስና ለማስረዳት ብቃቱም ሆነ ችሎታው የሌላቸው ጌታቸው በሻህውረድና ሻልቃ ማሞ "ካህናቱ የቤተክርስቲያንን ሀብትና ንብረት ለወያኔ ሊሰጡ ነው፤ ወያኔዎች ሆነዋል" በማለት የሚአስተጋቡትን ጩኸት እየሰሙ "የለንደንዋ ማርያም አድኑኝ ትላለች" በማለት የጻፉት ለቁምነገር አይመችም። ሐሰት ነው፤ ለቀልድም አይመችም በሃይማኖት ቀልድ የለም።

እንድርስዎ ያለ ዶክተር የሂሳብ አያያዝና የንብረት አጠባበቅ የላቀ እውቀት ያለው ቀረብ ብሎ ግራ ቀኙን ጠይቆ፣ ጉድለቶችን መርምሮ፣ ሀብትና ንብረቱ በአግባቡ እንዲጠበቅ የእርማትና የማስተካከያ ሐሳብ በመስጠት ቤተክርስቲያንን መርዳትና መተባበር የእምነት፣ የታሪክና የሀገራዊ ተግባር ግዴታ ሆኖ ሳለ ሌሎች የሀብት፣ የንብረትና የገንዘብ ፍቅር ያደነዘዛቸው፣ እውነት በአንደበታቸው

የጠፋባቸው፣ ጠዋት የተናገሩትን ማታ መድገም የማይችሉ የጮኹትን የሐሰት ጩኸት ተቀብሎ ያለ መረጃና ያለምስክር የቤተክርስትያን በር የሚከፍቱትን፣ ምእመናንን የሚአስተምሩትንና የሚአጽናኑትን፣ የተወለደ የሚአጠምቁትን፣ የሞተ ጸሎተ ፍትሐት አድርሰው የሚሸኙትን፣ ለሀገር ሰላም ለወገን ፍቅር የሚጸልዩትን ካህናት ፎቶግራፍ ከነመንፈሳዊ አርማቸው በመለጠፍ መርዛማ በሆኑ ቃላት ስም ማጥፋት፣ በሐሰት መፎከር "ሳያረጋግጡ ወሬ፣ ሳይገድሉ ጎፈሬ"።

ቸር ይግጠመን

Ewnet Beqalu